# ጀግና ምን ጊዜም ጀግና ነው

## ከቦስተን ሰሜን አሜሪካ

### *በአሜሪካ የመሸገው የፀረ ህዝብ ኋይል ቡቹሎች ቅስም የሰበረ የትግራይ ማኀበረሰብ ህዝባዊ ስብሰባ*

### *በኦገስት 14, 2016 ከ2 እስከ 5፡30 ፒ ኤም በቦስተን ከተማ በደመቀ ሁኔታ ተካሂዷል*

*በስብሰባው የተገኘው በቦስተንና አካባቢዋ የሚኖረው የትግራይ ተወላጆች ማኀበረስብ ሲሆን ዓላማውም እንደወትሮው የህዝባችንና የሃገራችን ልማት፣ ደህነትንና ከዲሞክራሲያዊው ስርዓት ጋር የተያያዘው የመልካም አስተዳደር ጉዳይን የተመለከተ ነበር።*

*የዕለቱ የክብር እንግዶች ከትግራይ የመጡ የመንግስት፣ የፖለቲካ ድርጅትና የህዝባዊ ማኀበራት መሪዎች ሲሆኑ ደሊጌሽኑ ይዞት የመጣውን መልእክት ቢፓወር ፖይንት በተደገፈ ተራ በተራ ስለሃገራችን የመጀመሪያው አምትስ ዓመት የልማት እቅድ አፈፃፀም፤ የቀጣዩ አምስት ዓመት እቅድ፤ በውጭ የሚኖሮው ኢትዮጵያዊው ዲያስፖራ በሃገሩ ልማት ስለነበረው ተሳትፎ፤ በቀጣይም ዲያስፖራው በምን መስኮች በበለጠ ቢሳተፍ ሃገሩንም ራሱንም ሊጠቅም እንደሚችል በስፋት የተገለፀለት ሲሆን ተሳታፊው የተለያዩ ሃገራዊ፣ ልማታዊና ግላዊ ገጠመኞቹን በተመለከቱ ጉዳዮች ተራ በተራ ጥያቄውን በማቅረብ በተያዘለት የጊዜ ገደብ ውስጥ በተሰጠው በቂ መልስና ማብራሪያ በመርካቱ የስብሰባው አዳራሽ በጭብጨባና ሆታ ደስታውን የገለፀበት የተዋጣለት ህዝባዊ-ሃገራዊ የስብሰባ ዕለት ነበር።*

*የዚህ መሰሉ ስብሰባዎች በሰሜን አሜሪካ በሚገኙ ከተሞች በየዓመቱ የሚካሄድ ሆኖ ስብሰባውን የሚያዘጋጀው በሰሜን አሜሪካ የትግራ ተወላጆች ማኀበር ነው። ይህ ማኀበር 42 ዓመታት ያስቆጠረ የታጋዮች ማኀበር ሆኖ የተዋቀረውም የትግራይ ህዝብ በንጉሰ-ነገሥቱ ስርዓት ይደርስበት ከነበረው ሁል አቀፍ ጭቆና ለማላቀቅ ታግሎ ማታገልን ነበር። ከደርግ መፈጠር ማግስት ጀምሮም ከህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ ጎን በመሰለፍ እስከ የደርግ ህልፈተ ውድቀት ድረስ በሰሜን አሜሪካ የሚኖረው ህዝባችንን በማስተባበር ደርግን ለመጣል ታግሏል፣ ኣታግሏል። በአሁኑ ወቅትም ቀንደኛው የህዝባችን ጠላት በሆነው ድኅነት ላይ ለመዝመት የአሜሪከው ነዋሪ ህዝባንች ከድሉ ማግስት ጀምሮ ባደራጃቸው በተለያዩ የልማት ማኀበራት በመሳተፍ ሌት ተቀን ሰርቶ ያፈራውን ገንዘብ በሀገሩ ልማት  በማዋል ላይ ይገኛ። መፈክሩ ወያኒያዊ ነው፣ የትግሉ ግብም ድኅነትና የፀረ ህዝብ ኃይል ሙሉ በሙሉ እስኪጠፉ ድረስ አጠናክሮ መቀጠል ነው። አሜሪካ የፀረ ህዝቦች መናሃሪያ ሳትሆን የኢትዮጵያውያን ታጋዮችና የህዝባችን ወገኖች የሚስተናገዱባት፤ የህዝባችን ባህል፣ ልምድ፣ ወግና እድገት የሚንፀባረቅባቸው መድረኮች የሚዘጋጁባትና የህዝብ ለህዝብ ግኑኙነት የሚያጠናክሩ ስራዎች የሚሰራባት ሃገር ማደርግ ነው።*

*ኦስገት 14, 2016 በቦስተን ከተማ የተካሄደውን የስብሰባ ውጤት ከማጠቃለሌ በፊት ለመግለፅ የምፈልገው ጉዳይ 1) እኛ በሰሜን አሜሪካ የምንገኝ የትግራይ ማኀበረሰብም ሆን የምንታገልለት ህዝባችን ሰላም ወዳድ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ በአጠቃላይና እያንዳንዱ ብሄር፡ ብሄረሰብና ህዝብ በተናጠል እንደራሱ በእኩል ዓይን የሚያይ፣ የሚያከብር፣ የሚወድና ትርፍ ቃል የማይወጣው ትሁት፣ኩሩ ህዝብ መሆኑን ላሰምርበት እንወዳለሁኝ፤ 2) በአንፃሩም ህዝባችን እንደህዝብ ከፍና ዝቅ ለማድረግና ከሌላው ኢትዮጵያዊ ወገናችን ጋር አለ አስፈላጊ ግጭት ውስጥ ለመክተት ደፋ ቀና የሚለውን የኋላ ቀር ስርዓቶች ናፋቂና ፀረ ህዝብ ኃይል ከሌላው ሰላም፣ እድገትና ፍቅር ፈላጊው ኢትዮጵያዊው ወገናችን ጋር በመሆን ከነመሰረቱ ለማድረቅ እንደ ወትሮው በትግል መስመር መሆናችንን መገንዘብ አስፈላጊ መሆኑን፤ 3) ሌላው ኢትዮጵያዊው ወገናችን ለመግለፅና እንዲረዳልን የምንፈልገው የትግራይ ህዝብ ጠላቶች ታጋዩ ህዝባችን "ወያኔ"፡ "ኢጋሜ" እያሉ እየሰደቡ እየመሰላቸው ሳያውቁ እያደነቁት፣ እያደነቁን ስለመሆናቸውን ነው። "ወያኔ" በአማርኛው የሚገለጽ ቃል ሆኖ በመነሻው ቋንቋ ትግሪኛ "ወይን" እና "ወያናይ" ማለት ነው። "ወይን" ማለት "ተነስ ታገል"  ማለት ሲሆን "ወያናይ" ማለት "ታጋይ" ማለት ነው። ስለዚህ የትግራይ ህዝብ ትግል እና ታጋይነት የሚገልጽ ሲሆን የጠላቱ ኃይል እየሰደበን መስሎት ታጋዩ ህዝብ ሲያደንቅና የትግል አርማችንና መጠሪያችን በበለጠ እንዲስተጋባ ማድረጉ ታሪካዊነቱና ዝክሩ ዘለዓለማዊ ያደርገዋል ባይነኝ። የትግራይ ህዝብ ከጥንትም ጀምሮ ለጠላት አልበገር ባይና የሃገሩን ግዛታዊ ክልል በመጠበቅ የሚታወቅ ጀግና ህዝብ እንደመሆኑ ወያኔ ነበር፣ ወያኔም ነው፣ በወያኔነቱም ይቀጥላል።* ***ታጋይ ምን ጊዜም ታጋይ ነውና።***

*ወደ የእለቱ ኣጀንዳ ልመለስና ባለፉት 25 ዓመታት ካለፈው አገዛዝ መገርሰስ ማግስት ጀምሮ በዚሁ ባለንበት ሰሜን አሜሪካ ስናየውና ስንታገለው የቆየን ክስተት የለውጡና እድገት ፈላጊው ወገን ሃገሩ ለመገንባ ላይ ታች ሲል ፀረ ህዝብ አጀንዳ አንጋቢው ደግሞ የሚገነባውን እንዲቆም ወይም እንዲፈርስ ሲቀሰቅስና በዘረኝነት አጀንዳ ተጠምዶ የጠላቶቻችን ዘበኛ በመሆን ሰበብ ኣስባብ እየፈለገ እርስ በራሳች እንድንቃቃር፡ እንድንጠራጠር  ከተቻለውም እንድንተላለቅ ያላዋቀረው ድርጅት፣ ያልፃፈው ጽሁፍ፣ ያላስተላለፈው መልእክትና ያላካሄደው ቅስቀሳ አልነበረም። የጠላቱ ኃይል ጥረት ሳምንታት ሳያስቆጥር እየመከነበት ለራሱም ይሁን ለሌው የፈለገውን የስልጣ መቆናጠጫ ብሎ ሲያልመው የነበረው ሁከትና ብጥብጥ ሳይሳካለት በታጋዩ ኃይሉ አሸናፊነት  ህዝባችንም ሆነ ሃገራችን በልማት ጎዳና ላይ ናቸው።*

*ኦገስት 14, 2016 በቦስተን ሰሜን አሜሪካ በተካሄደው የስብሰባ ቦታ ላይ የተከሰተውም ከላይ እንደተገለፀው ነበር። በቦስተንና በአካባቢዋ በሚገኙ ከተሞች የሚኖሩ የትግራይ ተወላጆች በተጠራው ኣጠቃላይ ስብሰባ  ከትግራይ በመጡ የእለቱ የክብር እንግዶች ሊጀመር ሲል የዝባችን የጠላት ወገን ቡቹሎች የስብሰባው አዳራሽ ገፍትረው ለመግባትና ስብሰባውን ለማደናቀፍ ሙከራ ሲያደርጉ ተሰብሳቢው ወንዱም ሴቱም፣ ወጣቱም አዛውንቱም በኅብረት ከትክቶ በማስወጣት በርቀት እንዲሸሹ ሲያደርግ በተሰብሳቢው ይታይ የነበረው የደስታ ስሜት ለመለካት በሚያስቸግር ሁኔታ ነበር።*

*ስብሰባው ከ 2 እስከ 5፡30 ከሰዓት በኋላ በታቀደው ጊዜ ሳይስተጓጎል በከፍተኛ የደስታ ስሜት በሚያንፀባርቁ ጭብጨባዎችና እልልታዎች እየታጀበ  በተካሄደበት ወቅት ስብሰባውን ለመበተን አልሞ የተሰባሰበው የጠላት ሰልፈኛ ከህንፃው በርቀት በፖሊሶች ተገድቦ እንደለመደው ጉሮሮው እስኪደርቅ ድረስ የዘረኝነት ስሜት የሚገልፁ ስድቦችና እርግማኖች ሲያሰማ ዉሎ ሓፍረቱንና ድብደባውን ተከናንቦ ተበትኗል። ኣፍራሽ፣ በታኝና ከፋፋይ ፀረ ህዝብ ኃይል አንገቱን ቀና ባደረገ ቁጥር የህዝባችን አንድነት በበለጠ እየተጠናከረ የሚሄድ ስለመሆኑ ማንም ሰው ሊረዳው ይገባል። በራሳችንና በዝባችን ላይ ያነጣጠረው የጠላት ኃይል ዘመቻ በኅብረት ልንመክተው ግድ ይላል።*

*የእለቱ ተሰብሳቢም ከምን ጊዜም በበለጠ ብሄራዊ አንድነቱን አጠናክሮ ሁለገብ ትግሉን እንደሚቀጥልበት ቃል በመግባትና የታጋዮች ኅብረት መግለጫ የሆነውን ዘፈን "እኛ ወያኔዎች ነበርን፣ አሁንም ወያኔዎች ነን፣  ለወደፊትም ወያኔዎች ነን" እያለ በመዝፈንና ደስታውን ለመግለፅ በመሳሳም የእለቱን ስብሰባ በከፍተኛ ህዝባዊ - ወገናዊነት በሚያንፀበርቅ ሁኔታ ተጠናቋል።*

*የዘረኞች እጣ ደርቆ መጥፋት ሲሆን*

*ሰላም ወዳዱ ህዝባዊ ኃይላችን ምን ጊዜም የድሎች ባለቤት ነው*

*በማንተመ ፍስሃ*

*የስብሰባው ተሳታፊ*